# መርህ አልባ የፍልስፍና ናፋቂዎች

መቼስ ዓለማችን በየጊዜው ከሚያጋጥሟት የተለያዩ ፈተናዎች ለመውጣትና የሰው ልጅን ጨምሮ በውስጧ ላሉትን ፍጥረታት የምትሰጠውን አገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ፍልስፍና እንዲሁም በተለያዩ ወቅቶች በፍልስፍና የተገኙ ግኝቶችን ተጠቅሞ መጓዝ ለነገ የማይባልበት ጊዜ እንደምንገኝ በማንኛውም አካል ሊታወቅ ይገባል፡፡

ዓለማችን መቼ እንደተፈጠረች በራሱ የተለያዩ የስነ ምድር ፈላስፋዎች የተለያየ መላ ምት ይሰጣሉ፡፡ ፍልስፍና በምድራችን መች ተጀመረ የሚለውን ጥያቄ ሲመጣ ደግሞ የበለጠ አከራካሪ ያደርገዋል፡፡ አንድ እውነት መናገር ግን ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም ከልደተ ክርስቶስ በፊት ዓለማችን የተለያዩ ፈላስፋዎችን እንዳስተናገደች የሚመሰክሩ የተለያዩ የሰው ስራ ውጤቶች መገኘታቸውን መመልከት ይቻላል፡፡ ቢሆንም ግን ይህ የተከበረ ስራ በተለያዩ መንግስታት ሲወገዝ፣ በተለይ ደግሞ ለስልጣናችን አደጋ ነው በተባለበት ሁኔታ ፈላስፋዎቹ የገቡበት ተገብቶ ስራዎቻቸውን እንዲለውጡ ወይም ደግሞ እንዲገደሉ በመገደዳቸው የተፈለገውን ውጤት አምጥቷል ቢባልም በታሰበበት ሁኔታ ተግባራዊ ሆኗል ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡

በኢትዮጵያ ፍልስፍና መች ተጀመረ? አሁንስ ምን ላይ ይገኛል? በምንልበት ግን ሁለትና ከዛ በላይ ተቃራኒ ሁኔታዎች እንደምንመለከት አያጠራጥርም፡፡ በተለይ ባለንበት ዲሞክራሲያዊ ዘመን የተሰጣቸውን ነፃነት በመጠቀም በኩል እራሳቸው በራሳቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ፈተና የሚጋረጥባቸው የፍልስፍና ተቋማት ማየት ደግሞ በበለጠ መልኩ አግራሞትን ይጨምሯል፡፡

ቀደም ብየ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ፍልስፍና ከልደተ ክርስቶስ በፊት ሲጀመር የራሱ የሆነ መርህ( ፅንሰ ሐሳብ) ይዞ በመጓዝ ባለሞያው ያመነበትን ከመናገር ወደኋላ የሚልበት አንድም ነገር አልነበረም፡፡ ፍልስፍናው በሌሎች ተቀድሞ የበለጠ ግኝት እስካልተገኘ ድረስ በራሱ ዓለም ላይ የመሰለውን ይናገራል፣ ይሆናል ያለውን ሐሳብ ያራምዳል በዘመኑ በነበሩ መንግስታት ሐሳቡን እንዲለውጥ በሚገደድበት ጊዜም ሐሳቡ ከሚሻር ይልቅ ህይወቱን መስዋእት ማድረግ ስለ ሚመርጥ መስዋእት ሆኗል፡፡

በሃገራችን የሚስተዋለውን መርህ አልባ የፍልስፍና አረማመድ በመተው አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የፍልስፍና መርህ ከህዝቦች ጥቅም ይልቅ የአገሮች ደህንነት፣ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲሁም ርእዮተ ዓለምን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የተገደደ ይመስላል፡፡ ለዚህ ቁልፍ ማረጋገጫ ደግሞ ፍልስፍናም እንደ ስርዓቱ ግራዘመምና ቀኝዘመም የተባለ እስኪ መስል ድረስ የምስራቅና የምዕራብ ፍላስፋዎች እየተባለ ጎራ ከመለየት በተጨማሪ አንዱ ያገኘውን ግኝት ሌላው ከማጠናከር ይልቅ ለማፍረስ የሚሽቀዳደምበት ጊዜ ላይ የደረስን በመሆኑ የዚህ ቅዱስ ተግባር ተጠቃሚዎች የነበሩ ህዝቦች ግራ የተጋቡ ቢመስሉም በቆሙለት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከማመን ግን ላንዴም ወደኋላ ብለው አያውቁም፡፡

ይህን ያክል ከተናገርኩኝ በጣም አሳሳቢ ወደ ሆነብኝ የሃገራችን ሁኔታ ከመሸጋገሬ በፊት በዓለም ታሪክ ላይ የሚዲያን ፍልስፍና ሁኔታ ላስነብባችሁ ላሰብኩት ርእስ የራሳችሁን አስተያየት እንድትሰጡና የጎደለኝን ነገር በበለጠ እንድትሞሉበት ትንሽ ጫርጫር ላድርግ፡፡ በ15ኛና 16ኛ ክፍለ ዘመን የህትመት ሚዲያዎች በአውሮፓ መታተም ሲጀምሩ የኮሙዩኒኬሽን ጦርነት(war of communication) እስከ ማለት የተደረሰበት ጊዜ በመሆኑ ግብረ ገብ

የጎደላቸው የህትመት ውጤቶችን ለመቆጣጠር ሳንሱር እንዲካሄድ ያስገደደ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበረ፡፡ በ19ክ/ዘ ግን ይህ አስተሳሰብ የሚያስለውጥ ሁኔታ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ተፈጠረ፡፡ በመጠኑም ቢሆን በኢንዱስትሪ እድገት ላይ የሚገኙ ህዝቦች የትምህርትና የምርምር ሁኔታዎቻቸው እየዳበረ በመምጣቱ የህትመትን ስራ በገደብ ሳይሆን የሃገርን ጥቅም እንዲያስቀድሙ በማስተማር ሳንሱር የሚል አስተሳሰብ ከሚድያ በማስነሳት የተለያዩ የምርምር ውጤቶች የያዙ መፃህፍትን ጨምሮ ጋዜጦችና መፅሄቶች እንደ ፍላጎታቸው ውጤታችው እንዲያስብቡ እንዲነበቡ የሚፈቅድ በአሜሪካ "The 1791 First Amendment" የሚለው አዋጅ ተጀምሮ በመላ አውሮፓ ለማስፋፋት ዕድል አግኝቷል፡፡ ይህን ተከትሎ ነው እንግዲህ የማስሚዲያ ዘመን(The age of mass media) ተብሎ የሚታወቅ ዘመን ከ1930ዎቹ ጀምሮ ተፈላጊነቱ እየጨመረ የሄደው፡፡ በነዚህ የመጀመርያ ጥቂት ዓስርት ዓመታት ሚሪያዎች በፖለቲካ ተፅዕኖ የተቸገሩ በመሆናቸው የርዕዮተ ዓለም ዘመን(Age of Ideology) ተብሎ እንዲታወቅ ግድ ሆኗል፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ቢኖር ሚዲያዎች ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ አንስተው የተጠመዱበት ተግባር በየፊናቸው የሚገኙበትን ስርዓት የማስቀጠል ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የግልም ይሁን የህዝብ ሚድያዎች የሚያራምዱት ርእዮተ ዓለም ሃገራቸው ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ክሊስቶን አር ኮፕስ የተባለ አሜሪካዊ "Hollywood Goes to War" በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዳስነበበው ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ይቅርና በፊልም ስራ ላይ የተሰማሩ የሆሊውድ ባለ ሞያዎች ሳየቀር በውጊያ ጊዜ በጠላታቸው ላይ የደረሰውን ሽንፈትና በየቀኑ የምዕራብ ወታደሮች የሚያገኙትን ድል ፅንፍ ላይ አስቀምጠው ፊልም በመስራትና በማሰራጨት እንዲሁም በካፒታሊዝም ተከታዮች

የሚታይ የህዝቦች ነፃነትና በኮምኒዝም የሚታየውን ስቃይ በህዝቦች መንፈስ ላይ በማስረፅ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ይላል፡፡

ስለዚህ ሚዲያ በማንኛውም ጊዜ ከመንግስት ጋር ያለውን ጥላቻ ወይም ክብር የሚገልፅ ተለጣፊ ሳይሆን የራሱ ፍልስፍና መከተል ይኖርበታል፡፡ ቢሆንም ግን የሃገሪቱን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍልስፍና ወደ ጎን መተው የለበትም፡፡ መርህ አልባ የፍልስፍና አራማጆች በማለት ለፅሁፌ እንደ መነሻ እንድጠቀምበት ያስገደደኝ ነገር ታዲያ የአገራችን የግል ሚዲያዎች ደጋግሜ ትዝብት ላይ ካስቀመጥኩ በኋላ ነው፡፡ በእርግጥ በማነኛውም መልኩ ሚዲያዎች ሲቋቋሙ የመጀመርያ ግባቸው የተቋቋሙለትን ዓላማ ማሳካት ነው፡፡ የግል ሚዲያዎች ዋና ዓላማ ደግሞ የንግድ በመኑ ግባቸው ትርፍ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ቢሆንም ግን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገር ጉዳይ ላይ መደራደር አይገባቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም የሃገሪቱ ዜጋ ነገና ከዚያ ወዲያ ተረጋግቶ የህትመት ውጤታቸው ሊገዛላቸው የሚችለው በሀገር ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር ላይ ሚዲያዎች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ደግሞ ማንም የሚገነዘበው ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ቀደም ብየ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ሚድያዎች የየራሳቸው ፍልስፍናና የፍልስፍና መርህ ቢኖራቸውም የሀገራቸውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሰረት ያደረገ መርህ እንደሚከተሉ ለማሳየት የሆሊውድ ፊልም ተቋም ሳይቀር ምን እንደሰራ ጠቂሻለሁ፡፡ አሁን ደግሞ በሁለቱ ማለትም ግራ ዘመምና ቀኝዘመም በሚባሉ አስተሳሰቦች የግልና የመንግስት ሚድያዎች አጠቃላይ ሚናቸው በሁለት ከፍሎ ያስቀምጧቸዋል፡፡ ይህም ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣትና ስርዓትን ለማስቀጠል መሆኑ ነው፡፡ እዚህም ላይ ትንሽ ለመናገር ያክል እንደነ ቪ .ኦ .ኤ እና ቢ. ቢ. ሲ የመሳሰሉ የህዝበና እንደ ሲ. ኤን. ኤን የመሳሰሉት ትላልቅ የግል ሚዲያዎች የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ በመዕራቡ ዓለም ህልውናው ካቆመ የህልውናቸውም ጉዳይ አደጋ ላይ

ስለ ሚወድቅ ሊበራል ስርዓቱ እንዲቆይ ብቻ ሳይሆን ያለውም ተፀዕኖ እየሰፋ እንዲሄድ አበክረው መስራታቸው የማይቀር ብቻ ሳይሆን ይረባራቡበታልም፡፡ አንድ ምሳሌ ለማስታወስ ባለፈው ጊዜ የምዕራቡ ዓለም የፋይናንስና የኢኮኖሚ ቀውስ ሲደርስባቸው እያዩ ዝም በሎ ከማለት አልፈው በመንግስታት ደረጃ አደጋው ይፋ ከተደረገ በኋላም እንኳ ቢሆን ካፒታሊዝም የሚነሳበት መንገድ ካልሆነ በስተቀር ለመውደቁ ምክንያት የተበላሸ የገንዘብ ስርዓት ነው ለማለት ሙሉ በሙሉ አልደፈሩም፡፡  በሌላ በኩል በህንድና በብራዚል የሚገኙ የመንግስትና የግል ሚድያዎች ደግሞ ሊበራል ስርዓት በሀገራቸው ከገባ የህዝባቸው ነፃነትና የተጠቃሚነታቸው ጉዳይ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ በመገንዘብ  ልማታዊ መንግስት እንዲያንሰራራ ሌት ተቀን በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ምሳሌ ህንድ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ተቋም በመመስረት ግምባር ቀደም አገር ናት፡፡ ይህ ተቋም ዋና ስራው በሃሪገቱ የሚፈጠሩ አዳዲስ ታሪኮችን ማጉላትና ህዝቦች በሚፈጠርላቸው ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስት ተጠቅመው የሚያመጧቸውን ለውጦች በማየት በቀጣይ ለበለጠ ውጤት እንዲሰሩና በሀገሪቱ ያለው ድህነት በማጥፋት (ስር ነቀል ለውጥ) ለማስመዝገብ እንቅልፍ አጥተው እንዲሰሩ ማነሳሳት ነው፡፡

የአገራችንን አንዳንድ የግል ሚዲያዎች በምታዘብበት ጊዜ ደግሞ ለሌላ ህዝብ ይቅርና ለራሳቸው ማሰብ የተሳናቸው እስኪ መስሉ ድረስ ሲኳትኑ ይስተዋላሉ፡፡ የዚህ ድምር ውጤት የህዝቡ ንቃተ ህሊና እየጎለበተና የመተንተን ዓቅሙ በሚያድግበት ወቅት ዕጣ ፋንታቸው ውድቀት መሆኑ ባይዘነጋም በአሁኑ ወቅት ግን በመርህ ለሚጓዙ ጋዜጠኞችን ገበያ ሲሻሙ ይታያሉ፡፡

ለፅሁፌ መነሻ የሆነው ጉዳይ ሁሉም የግል ጋዜጦች ከመርህ ውጭ ናቸው ባልልም በአብዛኛው አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ በሰፊው ይስተዋላል፡፡ በዚህም መርሃቸው ምን ይሆናል ስል ለማውጠንጠን ስለ ተናሳሁኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሌ የሚሮጡት

ከፀና አቋማቸው ሳይሆን ከሚያገኙት ትርፍ አንፃር በመመዘን ነው፡፡ ጋዜጦቹ በየፊት ገፆቻቸው የሚፅፏፏቸው መርህ መሰል መፈክሮች በደዛዛው ሲቃኙ ለዚች አገር የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የሚሰሩ ያስመስላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ መፈክሮች እንደመጣላቸው የሚፅፉ አንዳንዶቹ ደግሞ ለጋዜጣቸው ጥሩ ስም እንስጥ ከሚል ግልብ ሀሳብ በመነሳት በፊት ገፅ ላይ የሚለጥፉ ናቸው፡፡ምሳሌ "**ነጻ ሃሳብ ሚዛናዊ መረጃ፣ ነፃ መረጃ ነፃ ኢኮኖሚ ነጻ ሕዝብ፣ ነጻ ፕሬስ ነጻሃሳብ ነጻመንፈስ፣ የምንፈራው ውሸትን ብቻ ነው**" የሚሉ በሚታይበት ወቅት በዚች አገር የጋራ መግባባት ላይ የሚሰሩ ያስመስላቸዋል፡፡ ውስጣቸው ሲታይ ግን እንኳንስ ህዝብን ወደ አንድ አስተሳሰብ ለማምጣት ቀርቶ ተመሳሳየ ሃሳብ ለማስጨበጥ ያልቻሉ መሆናቸውን ከሚያዋቸው ዘገባዎች ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ቀደም ብየ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የሚድያዎች ሚና ስርዓትን የማስቀጠል ወይም ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት መሆኑ ለመግለፅ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ታዲያ የአገራችን ሚዲያዎች ከየተኛው መፈረጅ ይቻል ይሆን? የፍልስፍናቸው መነሻ የት ነው? ተብሎ ሲጠየቅ ንፋስ ባመጣላቸው ይጮሃሉ ከማለት በስተቀር ሌላ ነገር ለማለት የሚቼል አካለ የሚኖር አይመስለኝም፡፡ ለምሳሌ በዘንድረው ዓመት ብቻ የታዘብኩትን ማቅረብ በቂ ይመስለኛል፡፡ እዚህ ላየ ሃይማኖትን በተመለከቱ ጉዳዮች ጠባብና የከሰሩ ፖለቲከኞች ሊያሰኬዱት ለሞከሩት ስራ ሳያጅቡላቸው በፅናት በመቆማቸው ከልቤ አደንቃቸዋለሁ፡፡ በሌላ በኩል ግን ጋዜጦቹ የፓርቲ ልሳን እስኪመስሉ ድረስ ቆመው መቅረታቸውን ስመለከት ደግሞ ከልቤ አዝናለሁ፡፡ የዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ በኢዲቶርያል ፖሊሲያቸው ያለ ክፍተትና ስራውን ሲጀምሩ የት ለመድረስና በምን መልክ መሄድ እንዳለባቸው የሚያሳይ ወጥ የሆነ የፍልስፍና መርህ የሚጎድላቸው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ይሰራሉ እንዳይ ባሉ አይፈልጉትም፣ ስርዓት ለማስቀጠል ይሰራሉ እንዳይባሉ

ደግሞ የሚፈልጉት ስርዓት በየትም ዓለም ያለ አይመስልም፡፡ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ አካሄዳቸው በተናጠል ሳይሆን ባንድ አርእስት ላይ እንደ ዘመቻ ሲያስኬዱት መስተዋሉ ነው፡፡

እዚህ ላይ ዘንድሮ በአገራችን የተከሰቱ ዓበይት ክንዋኔዎች ናንሳና ባገራችን የግል ሚድያዎች የተሰጣቸውን መላ ምት እንመልከት፡፡ መቼስ ሁላችንም ለማየት እንደምንችለው አገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደራራቢ ድሎች እየፈጠረችና መልካም ዕድሎች እያገኘች ናት፡፡ የዚህን ውጤትም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ለኢትዮጵያ የሰጧት ስም መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ ሮይተርስ የተባለ የዜና ወኪል “ ኢትዮጵያ ለተከታታይ 10 ዓመታት የ10% ዕድገት አስመዘግባለች” ሲል ቢቢሲ በበኩሉ የግልገል ጊቤ ሶስትን ፕሮጀክት በዘገበበት ወቅት “የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ ጫና ለመፍጠር ብድር ቢከለክልም የግድቡ ግንባታ ወደኋላ በማይመለስበት ደረጃ ደርሷል” ብሏል፡፡ የሃገራችን የግል ሚድያዎች ግና የሚሽቀዳደሙት መጥፎ መጥፎውን ለመዘገብ እንዲሁም በሁሉም መንገድ መንግስትን ለመቃወም በመሆኑ እነዚህን መለካም ሁኔታወችን በመተው በገፅታ ግንባታችን ላይ በሚዘምቱብን ድርጅቶች ድረገፅ ሲያነፈንፉ ይውላሉ፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ኢትዮጵያ እየሰራች ያለቺው በገጠርና በከተማ ህብረተሰቡን ያሳተፈ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ በዚህ ጉዞዋ ደግሞ በጣም ብዙ የሚባሉ ትልልቅ መልካም ተሞክሮዎችና ድሎችን አስመስዝግባለች፡፡ ይህ ማለት ግን ካሁን በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር የለም ፣ ሁሉ ህዝብ አልፎለታል ፣ ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ማለት አይደለም፡፡ እንደ መንግስት የተያዘው ስትራቴጂም በቃኝ የማይልና ባለፈለት ቁጥር ሌላ ፍላጎት የሚጠይቅ ህብረተሰብ መፍጠር ነው የሚለው፡፡ ስትራቴጂውን እውን ለማድረግና የነገውን የህዝብ ጥያቄ ለመመለስም መንግስት በተለያየ ዘርፍ የተወሰኑ ክፍተቶች ቢኖሩትም በሙሉ ዓቅሙ በመስራት ላይ

ይገኛል፡፡ ከወዲሁግን ጥረቱ አዋጭ መሆኑ የሚያሳዩ ምልክቶችም በየጊዜው እየተነገረለት ይገኛል፡፡ ስትራቴጂው በታዳሽ ሃይል መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተስፋው የላቀ ያደርገዋል፡፡

በዚህ በኩል ታዲያ ፈተናዎች የሉም ማለቴ ሳይሆን የግል ሚዲያዎች ከሚናገሩት ግን ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ በመሆኑ ሊገናኝም አይችልም፡፡ በተለይ በገፅታ ግንባታ አኳያ ስንመለከት “የገፅታ ግንባታ ከራስ ይጀምራል” የሚለውን አባባል እንኳ አያስተውሉትም፡፡ አገራችን በተደጋጋሚ በበጎ ገፅታ ስትነሳ ቆይታ የመብራት እጥረት በተከሰተ ወቅት ጋዜጦች በተደጋጋሚ ያስነብቡት የነበረው አንድ ሰው አዲስ አበባ እንዳይመጣ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ እስከ ሚመስሉ ድረስ “አዲስ አበባ በጨለማ ተውጣለች” የሚሉ ፅሁፎች በፊት ለፊት ገፃቸው በማስፈር ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ የግልገል ጊቤ ሦስትን ግድብ አንስተው ኬንያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ልትከፍት ትችላለች በማለት መጥፎ ምኞታቸው አስነብበዋል፡፡ የኬንያና የኢትዮጵያ ጋዜጦች ስለ ግልገል ጊቤ ሦሥት አነሰተውና  ችግር አለ ብለው የተናገሩት ብዛት ቢሰላ ከ80% ባላነሰ መጠን የኢትዮጵያ ፕሮጀክት ያጣጣሉት የኢትዮጵያ ጋዜጦች ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ በአንፃሩ ግን በግልገል ጊቤ ፕሮጀክት መዝመት ማለት በአገር ጉዳይ መዝመት በመሆኑ አንደራደርም ሌላ ካለ እንጂ ግልገልጊቤ የነገ ተስፋችን በመሆኑ መንግስት እሰየው እንኳን ሰራህ ያሉ ጋዜጦች ነበሩ፡፡ እነዚህ በአገር ጉዳይ ላይ አንደራደርም ማለታቸው ራሱ የሚያስመሰግናቸው ሲሆን በጣም ሊገፉበት ይገባልያስብላል፡፡ እንዲህ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ሳይሆን በውስጧ የሚገነቡ መሰረተ ልማቶችንና ዲሞክራሲያዊ ሂደትንም መደገፍ ይገባል፡፡

በመነሻየ ለመጥቀስ እንደ ሞከርኩት በየተኛውም ዓለም የሚደረግ የለውጥ እንቅስቃሴ የሚመራበት ፍልስፍና አለው፡፡ ፍልስፍናው ደግሞ እንደየ አገሮቹ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ሊለያይ ይችላል፡፡ በዚህ ውስጥ ግን ግለሰብም ቢሆን በሚቀጥለው ወር ወይም ቀን የት እንደሚውልእና ምን ላይ መድረስ እንዳለበት አልሞ ይንዛል፡፡ በአገራችን ያሉ የግል ጋዜጦች ግን መርሃቸው ምን እንደሆነ ሳያሳውቁ ንፋስ ባየለበት አቅጣጫ ለመንዝ በሚያደርጉት ትግል ከቀን ወደ ቀን ሲዘለፈለፉ ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህ ለመውጣት የራሳቸው ድርሻ ብቻ ሳይሆን የመንግስት እገዛ የሚያስፈልጋቸው ይመስለኛል፡፡

ቀጣዩ ጥረታችንና ስራችን መጪዋ ባለ ብሩህ ተስፋ ኢትዮጵያን እውን ማድረግ፣የሁላችን ተስማሚና ዜጎቿ ያለፈላቸው እንድትሆን በጋራ መስራትን የምትጠብቅ ናት፡፡ በመሆኑም ስለ ጭንቀትና ወቀሳ መፃፍን የሚቀናችሁ ጋዜጠኞች ምህረቱን ይስጣችሁ በማለት ለዛሬ ላብቃ፡፡ ሰላመ ሁኑሉኝ!

**በሚቀጥለው የ2001 የኢትዮጵያ የታዩ መልካም ተመኩሮዎች ላይ እንጌናኛለን**

ገ/ሄር ሙጉላት ነኝ ከአዲስ አበባ

For your comment contact me at gbsyhlu@yahoo.com